የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፹፭
አዲስ አበባ–ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9[th] Year No. 85
ADDIS ABABA–5[th] September, 2003

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺፭ ዓ·ም
የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፫፻፴፭

CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 91/2003
Higer Education Cost-sharing Council of Minsiters Regulation ................................................. Page 2335

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺፭
### ስለ የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት
### በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል ።

**፩· አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺፭ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪· ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ

፩· "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የትምህርት ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስትር ነው ።

፪· "ተቋም" ማለት በመንግሥት አካል ሥር የሚተዳደር ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ትምህርት የሚሰጥበትና በማንኛውም ክልል ወይም በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ከፌዴራል መንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ተቋም ነው ።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 91/2003*
### *HIGHER EDUCATION COST-SHARING*
### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION*

*This regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and the Hihger Education Proclamation No. 351/2003.*

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the ''Higher Education Cost-Sharing Council of Ministers Regulation No. 91/2003''

2. *Definitions*

For the purposes of this Regulation:

1) ''Ministry'' and ''Minister'' means Ministry of Education and the Minister of Education, respectively.
2) ''Institution'' means a public higher learning institution in any region, in Addis Ababa or Dire Dawa offering a post-secondary education with a budget allocated from the Federal Government.

፫· "አሠሪ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመራቂን ቀጥሮ የሚያሠራ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋምና ዓለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ድርጅት ሲሆን በሙያው በግሉ ሥራ የተሠማራ ሰውን ይጨምራል ።

፬· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ።

፭· "ተጠቃሚ" ማለት ማንኛውም በመንግሥት ተቋም ለመማር እና የሚፈለግበትን ወጪ ለመክፈል ከተቋሙ ጋር ውለታ ገብቶ የከፍተኛ ትምህርት ወይም ሥልጠና የሚከታተል ተማሪ ነው ።

፮· "ወጪ መጋራት" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚ እና መንግሥት ለትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ የሚጋሩበት ሥርዓት ነው።

፯· "ከምረቃ በኋላ ከገቢ ተከፋይ" ማለት ማንኛውም ተጠቃሚ በገባው ውለታ መሠረት የሚጋራውን የወጪ መጠን ከወርሃዊ ገቢው በታክስ መልክ እየቀነሰ የሚከፍልበት ሥርዓት ነው ።

፫·የደንቡ ተፈፃሚነት

ይህ ደንብ ከ፲፱፻፺፮ የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ ተቋማት በሚገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ካሉበት ዓመት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል ።

፬· የተጠቃሚው ድርሻና አፈጻጸም

፩· መንግሥት ለምግብና ለመኝታ የሚያወጣውን ወጪ ሙሉ በሙሉና ፣ ለትምህርት ከሚወጣው ወጪ ለመነሻ ከ ፲፭ ፐርሰንት ያላነሰ ተሰልቶ ተጠቃሚዎች እንዲጋሩ ይደረጋል ። ይህም ድርሻ በየተቋሙና በየመርሐ ግብሩ በሚወጣው ወጪ ላይ ተመስርቶ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በቅድሚያ ለተጠቃሚው መገለጽ አለበት ።

፪· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸውን መጠን ለመክፈል እያንዳንዱ ተጠቃሚ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከተቋሙ ጋር የጽሑፍ ውል በማድረግ፣ ትምህርቱን እንዲከታተል ይደረጋል ። ይህ የውለታ ሠነድ በሕግ ፊት የፀና ይሆናል ።

፫· ተጠቃሚው ትምህርቱን ካቋረጠ ወይም ካጠናቀቀ መክፈል የሚገባውን መጠን የሚያሳይ መረጃ በተቋሙ ይሰጠዋል ። ይህ መረጃ የተጠቃሚውን ሙሉ ስም፣ አድራሻ ፣ ፎቶና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን የያዘ ይሆናል ።

፬· ለተማሪው ትምህርትና ሥልጠና የሚወጣው ወጪ መጠን ቢያንስ በየሦስት ዓመቱ የሚከለስ ይሆናል ፣ ለዚሁም ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል ።

፭)·በታሳቢ ተምሮ ከምረቃ በኋላ ከገቢው ተከፋይ በሆነ መልክ እየተቀነሰ በገንዘብ ወይም በአገልግሎት የሚከፍል ተጠቃሚ በዜግነት ኢትዮጵያዊ መሆን ይኖርበታል ።

፭· ማበረታቻዎች

፩· በየዓመቱ የሚፈለግባቸውን መጠን ሙሉ በሙሉ በቅድሚያ በግል ወይም በድርጅቶች ድጋፍ ለሚከፍሉ ተጠቃሚዎች እስከ ፭ ፐርሰንት የሚደርስ ቅናሽ እንዲያገኙ ይደረጋል ፣

፪· ከተመረቁ በኋላ የሚፈልግባቸውን መጠን ሙሉ በሙሉ በተመረቁ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከፍለው ለሚጨርሱ ተጠቃሚዎች እስከ ፫ ፐርሰንት የሚደርስ ቅናሽ ይደረጋል ።

3) ''Employer'' means any government, private or non-governmental institution or international or regional orgnaization or person employing graduates of higher education institutions including self-employed graduate of the same,

4) ''Person'' means a physical person or any other legal person,

5) ''Beneficiary'' means a student at a public higher education institution pursuing higher education or training and who has entered into an obligation with the concerned institution for the future payment of the cost of his/her education or training and other services.

6) ''Cost-Sharing'' means a scheme by which all beneficiatries of public higher education institutions and the government share the cost incurred for the purposes of education and other services.

7) ''Graduate Tax'' means a scheme by which an amount is deducted from income in the form of a tax to be paid by a beneficiary who has been obliged to share the costs of his higher education.

3. *Scope of Application*

This Regulation shall apply to sutdents that are newly admitted to an institution beginning from 2003/04 academic year, as well as to students in their second year or above training during the 2003/4 academic year.

4. *Beneficiary's Share and Mode of Application*

1) All beneficiaries of public institutions of higher learning shall share full costs related with boarding and lodging and a minimum 15% of tuition related costs. The amount to be shared shall be calculated based on the cost to be incurred at each institution and programme of study and shall be revealed to the beneficiaries at the beginning of each academic year.

2) The beneficiary shall pursue his education after entering a written contract agreement with the respective institution for the future discharge of the amount of cost to be borne by him referred to under Sub-article (1) of this Article. This contract document is a legal document.

3) Any beneficiary who discontinues or completes his education shall be given a document stating the amount owed. The document shall have full name of the beneficiary, address, photo and other relevant information.

4) The cost of education and training shall be revised at least every three years. The Ministry shall enact directives to this effect.

5) Only an Ethiopian national is eligible for pursuing his higher education or training upon the contractual commitment for future payment, in cash or in service, of his share of the cost in the form of graduate tax.

5. *Incentives*

1) Up to 5% deduction of the payable cost shall be made for beneficiaries who pay every year the total cost determined either by themselves or by the support of organizations.

2) Up to 3% deduction of the payble cost shall be made for beneficiaries who pay the total cost determined within the first year of their graduation.

፫· ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በተመረጡ መስኮች ለመሠልጠን ፈቃደኛ የሆነ ተማሪ ከምረቃ በኋላ መንግሥት በሚመድበው ቦታ ሁሉ ቢያንስ ለሠለጠነበት ዓመት ሦስት እጥፍ ጊዜ ለማገልገል ውል እየፈረመ እንዲማርና ከተማረ በኋላ በገባው ግዴታ መሠረት አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

፬· ውል አፍርሰው የአገልግሎት ግዴታቸውን ያልተወጡ ተጠቃሚዎች ትምህርቱ የፈጀውን ወጪ በጊዜው ሥራ ላይ ባለው የድርሻ ክፍፍል (% ) የሚጠበቅባቸውን ከነወለዱ ቢበዛ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አጠናቀው እንዲከፍሉ ይገደዳሉ ።

፮· የወጪ ድርሻ አከፋፈል

፩· ተጠቃሚው ከምረቃ በኋላ ሥራ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ወይም ከምረቃ በኋላ ከአንድ ዓመት በኋላ የሚፈለግበትን ክፍያ ተቀጣሪ ከሆነ ከወር ገቢው በየወሩ ቢያንስ ፲ ፐርሰንት ከገቢ ተከፋይ በሆነ መልክ እየቀነሰ ወይም በሙያው በግሉ የተሠማራ ከሆነ ከዓመት ገቢው በዓመቱ የሚፈለግበት መጠን ተሠልቶ መከፈል አለበት ።

፪· ተጠቃሚው የሚፈለግበት ጠቅላላ መጠን የአገልግሎት ክፍያ ወይም ወለድ የሚከፈልበት ሆኖ ውለታ በተገባበት ወቅት በሀገሪቱ የሚሠራበት የተቀማጭ ወለድ መጠን ይሆናል ።

፫· ተጠቃሚው ያለበትን የክፍያ ግዴታ እንደ ትምህርት መርሃ ግብሩ ርዝመትና ዓይነት ከ፲፭ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ማጠናቀቅ ይኖርበታል ።

፬· ተጠቃሚው ትምህርቱን ሳይጨርስ በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥም እስካቋረጠበት ጊዜ የሚፈለግበትን ክፍያ መክፈል ይኖርበታል ። ሆኖም ትምህርቱን ያቋረጠው በሀገራዊ ጥሪዎችና ተልዕኮዎች ከሆነ ክፍያው መሠረዝ ይኖርበታል ።

፭· ተጠቃሚው ተቀጥሮ የሚሠራ ሲሆን ክፍያው በአሠሪው አማካኝነት በየወሩ ከደመወዙ እየተቀነሰ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል ። ሆኖም ይህ ተቀናሽ በማናቸውም ጊዜ ተጠቃሚው በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፰(፩) (ሐ) መሠረት ከፍ ካላደረገው በስተቀር ከገቢ ተከፋይ ተቀናሹ መጠን ከተጠቃሚው የወር ደመወዝ ፩/፫ኛ ሊበልጥ አይገባም ።

፮· ተጠቃሚው በውጭ ቅጥር ወይም በግል ሥራ ምክንያት በውጭ ሀገር የሚኖር ከሆነ ፣ ክፍያው የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን በሚያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ይፈጸማል ።

፯· አንድ በታሳቢ የተማረ ተጠቃሚ የሚፈለግበትን ክፍያ ሳያጠናቅቅ ከስድስት ወር በላይ ለሆነ ጊዜ ለመቆየት ወደ ውጭ አገር መሄድ ቢፈልግ ላልተከፈለው መጠን ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል ።

፯· የአሠሪዎች ግዴታ

፩· ይህ ደንብ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት የተከታተለን ሰው የሚቀጥር ማንኛውም አሠሪ የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩበታል ።

ሀ) ተቀጣሪው ከተማረበት ተቋም የተሰጠውን የሚፈለግበትን ክፍያ መጠን የሚገልጽ መረጃና በየወሩ ከደመወዙ እየተቀነሰ ገቢ ሊደረግ የሚገባውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የተሰጠ ማስረጃ እንዲያቀርብ የመጠየቅ ፣

ለ) የተቀጣሪዎችን ዝርዝር በ፫ ወር ጊዜ ውስጥ ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን በጽሑፍ የማሳወቅ ፣

ሐ) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ ፣ በቀረበለት መረጃ እና በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፰(፩) (ሐ) መሠረት ከተቀጣሪው ደመወዝ በየወሩ እየቀነሰ የማስተላለፍ ፣

3) Pursuant to directives to be issued by the Ministry from time to time, a beneficiary who volunteered to be trained in certain fields as designated by the government provided that he enter into a contract with the government to work in all places of assignment after graduation for at least three times the time spent in the training.

4.) Beneficiaries who, in breach of their agreement, refuse to discharge their obligation of service, shall be obliged to pay all outstanding cost of their training and education with interests, as per the rate applicable during the time of payment, within five years from the date of breach of their agreement.

6. *Mode of Repayment of Shared Costs*

1) The beneficiary shall start paying the amount within six months after graduation if earning income, or within a maximum of one year after graduation, in the form of graduate tax of at least 10% of the monthly income of an employee; or amount owed deducted from the yearly income if self-employed,
2) The total amount that a beneficiary is required to pay shall be subject to payment of service fee or interest, and the interest payable shall be determined pursuant to the deposit rate in use at the time of conclusion of the contract
3) Completion of repayment of amount owed by beneficiaries shall, depending on the type and duration of program, not exceed 15 years.
4) A beneficiary who discontinues his education due to any reason shall be required to pay the amount requird of him. However, in case the beneficiary discontinues education owing to national call of duty or service, the obligation to pay shall be waived.
5) In case of an employed beneficiary the amount owed shall be deducted from the monthly income of the beneficiary and transferred to the treasury by the employer. However, such deduction shall not exceed 1/3 of a monthly income without a prior consent of the beneficiary as per Article 8(1) (c) of this Regulation.
6) In case a beneficiary is living abroad as a result of private business or foreign employment, payments due shall be collected as per provision of an additional directives to be issued by the Federal Inland Revenue Authority.
7) A beneificary who decides to go abroad for more than six months before completing the payment of the cost required of him, shall be made to produce a gurantee for the payment of the outstanding amount.

7. *Obligations of Employers*

1. Any employer employing a beneficiary after the effective date of this Regualtion shall have the following obligations:-
   (a) to request a copy of the contractual agreement entered between the beneficiary and the Institution and a written document specifying the amount to be deducted from a monthly salary.
   (b) to forward to the Federal Inland Revenue Authority list of beneficiaries employed within a period of 3 months;
   (c) to deduct, and transfer every month, the amount owed by the beneficiaries as per Article 8(1) (c) of this Regulation and the Income Tax Proclamation No. 286/2002,

መ) ተቀጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) የተጠቀሰውን መረጃ ወይም ከዕዳ ክፍያ ነፃ መሆኑን የሚገልጽ ከፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን የተሰጠ መረጃ ካላቀረበ የተቀጣሪውን የወር ደመወዝ ፩/፫ኛ በመያዝ ሁኔታውን የማሳወቅና በፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን በሚያገኘው መግለጫ መሠረት ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መፍትሔ መስጠት ይኖርበታል።

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም አሠሪ ሳይሰበሰብ በቀረው ክፍያ መጠን እና ባልተከፈለባቸው ወራት በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል ።

## ፰· የተጠቃሚው ግዴታ

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮(፩) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀጣሪው በማናቸውም አሠሪ ተቀጥሮ ሲሠራ የሚከተለው ግዴታ ይኖርበታል ፦

ሀ) የሚሠራበትን ሙሉ አድራሻ ፣ እንዲሁም ከዚህ በፊት በሌላ ቦታ ሠርቶ ከሆነ ይህንኑ መረጃ ለአሠሪው በመስጠት በአሠሪው አማካኝነት ለፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን የማሳወቅ ፣

ለ) የሚፈለግበትን ክፍያ በየወሩ ከምረቃ በኋላ ከገቢ በተከፋይ መልክ ተቀናሽ በማድረግ መክፈል የመጀመር ፣

ሐ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬(፪) የገባውን የውለታ ሠነድ ለአሠሪው የመስጠትና አሠሪው ተገቢውን መጠን በየወሩ እየቀነሰ ለመንግሥት እንዲያስገባ የማድረግ ፣ ይህ መጠን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮(፩) ከተገለጸው ማነስ አይችልም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ (፮) የተመለከቱትን ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም ተጠቃሚ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል ።

## ፱· ዕዳን ስለመሠረዝ

ተጠቃሚው በውሉ መሠረት ግዴታውን ሳያጓድል ክፍያውን ሲፈጽም ቆይቶ ጠቅላላ ክፍያው ከመጠናቀቁ በፊት በጡረታ ቢገለል ወይም ቢሞት ቀሪው ብድር ይሠረዛል።

## ፲· የትምህርት ሚኒስቴር ሥልጣንና ኃላፊነት

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተለው ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል ።

ሀ) ይህ ደንብ ሥራ ላይ መዋሉን የመከታተልና የማረጋገጥ፣

ለ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ከተጠቃሚዎች የሚጠይቁትን የክፍያ ተመን የማጽደቅ ፣

ሐ) ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የማውጣት ፣

መ) የውለታ ሠነዶችን ይዘት የመወሰን ፣

ሠ) የወጪ መጋራቱ ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልግሎት የሚፈጸምበትን መስኮችና ዝርዝር መመሪያዎች የማወጣት ፣

## ፲፩· የፌዴራል ሀገር ውስጥ ገቢዎች ባለሥልጣን ሥልጣንና ኃላፊነት

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል ።

ሀ) ከእያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈለገውን መጠንና ወርሀዊ ክፍያውን ጭምር ለተጠቃሚውና ቀጣሪዎች የማሳወቅ፣

ለ) አጠቃላይ ክፍያውን የመሰብሰብ ፣ የመከታተልና የመቆጣጠር ፣

(d) If the employee has not produced the required documents as per Sub-Article (1) (a) of this Article or a document issued by the Federal Inland Revenue Authority, to hold one third of the monthly salary of the employee, inform the same to and give solution in a maximum period of three months based on the information of Federal Inland Revenue Authority

2. Any employer who fails to discharge all obligations set forth under Sub-Article (1) of this Article shall be liable for the amount not collected and shall be guilty of an offence for the month payment is not paid in accordance with the Income Tax Proclamation of the country.

## 8. *Obligations of the Beneficiary*

1) Without prejudice to provisions of Article 6(1) of this Regulation, a beneficiary employed by any employer has the following obligation:

(a) to inform the full address of his place of work and information pertaining to prior employment through the employer to the Federal Inland Revenue Authority;

(b) to start paying the amount required of him/her on monthly basis in the form of grduate tax;

(c) to submit the contract document entered as per Article 4(2) of this Regulation to the employer and assist the employer to withold part of his/her monthly salary and pay to the Government every month. The monthly payment shall not be less than the sum stipulated in Article 6(1) of this Regulation.

2) A Beneficiary who violates any of the obligations under Sub-Article (1) of this Article and those under Article 6 of this Regulation shall be liable in accordance with the Income Tax Proclamation.

## 9. *Cancellation of Payment Obligation*

The unpaid part of the cost of a beneficiary who has been discharging his payment obligation shall be cancelled in the event of death or retirement of the beneficiary.

## 10. *Powers and Duties of the Ministry*

Without prejudice to other provisions in this Regulation, the Ministry shall have the following powers and duties:-

(a) to oversee and ensure the implementation of this Regulation

(b) to approve the amount apportioned by higher education institutions from the beneficiaries.

(c) to issue, directives for the proper implementation of this Regulation.

(d) to determine on the substance of contractual document.

(e) to issue detailed directives on the areas and modalities of the cost shared in ways other than monetary.

## 11. *Powers and Duties of the Federal Inland Revenue Authority*

Without prejudice to other provisions of this Regulation, the Authority shall have the following powers and duties:

(a) to notify each beneficiary and employer the total amount of payment to be made by the beneficiary together with the monthly payment;

(b) to follow up, supervise and collect the total amount of payment to be made by the beneficiary;

ሐ) ለዚሁ ተፈጻሚነት አስፈላጊውን ሥርዓትና ድርጅት የመፍጠርና ተግባራዊ የማድረግ፣
መ) የሚፈለግበትን ክፍያ ላጠናቀቀ ተጠቃሚ ተገቢ መረጃ/ሠርቲፊኬት የመስጠት፣
ሠ) ለእያንዳንዱ ተጠቃሚ የግብር ክፍያ መለያ ቁጥር የመስጠት፣
ረ) በክልሎች ውስጥ ከሚቀጠሩ ተጠቃሚዎች የሚፈለገው ተቀናሽ መጠን ለመንግሥት ገቢ የሚሆን በትን ሁኔታ የማመቻቸት፣

፲፪· <u>የተቋማት ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

በዚህ ደንብ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋማት የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖራቸዋል ።
ሀ) የሥርዓቱን ተፈጻሚነት የመከታተል ፣
ለ) በየትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ተጠቃሚው እንዲጋራ የሚጠበቀውን ወጪ አስልቶ የመግለጽ ፣ ተጠቃሚውን በተመለከተ ተገቢውን መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ፣
ሐ) ከተጠቃሚዎቹ የሚፈለገውን ወጪ አጠናቅሮ ተጠቃሚው ከተቋሙ ሲለቅ አስፈላጊ መረጃ የመስጠት።

፲፫· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል

አዲስ አበባ ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

(c) to create the necessary procedures and organizational set ups/structure for the implementation of the foregoing;
(d) to issue certificate of completion of payment for the beneficiary who fully discharges his/her obligations;
(e) to issue a Taxpayer Identification Number for each beneficiary;
(f) to facilitate for the collection of the graduate tax from beneficiaries employed in regions.

12. *Powers & Duties of Institutions*

Without prejudice to other provisions in this Regulation, instiutions shall have the following powers and duties:
(a) to follow up the implementation of the cost sharing system;
(b) to notify the beneficiary, at the beginning of the academic year, the appropriate amount of cost the beneficiary has to share, and to keep record of all necessary data.
(c) to provide the beneficiary with documents stating the amounts that is to be paid by beneficiaries

13. *Effective Dates*

This Regulation shall enter in to force starting from the 12th day of September 2003.

Done at Addis Ababa, this 5th day of September 2003.

MELES ZENAWI

Prime Minister Of The Federal Democratic
Republic of Ethiopia